# የ1979-81 የሦስት ዓመት ዕቅድ የአዘገጃጀትና
# የአቀራረብ መመሪያ

ክፍል 1

# አጠቃላይ

የማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ
ኅዳር 1978 ዓ.ም

330.963
EPH

24

# የ1979-81 የሦስት ዓመት ዕቅድ የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያ

ክፍል 1

# አጠቃላይ

የእስታቲስቲክስ ፣ ጠ/ጽ/ቤት ፣
ቤተ ፣ መጻሕፍት ፣
C. S. O Library

የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ ኮሚቴ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ
ኅዳር 1978 ዓ.ም

## ማውጫ


ገጽ

ሀ. መ ግ ቢ ያ ................................ 1

ለ. አጠቃላይ የኢኮኖሚና የበሻለ ሁኔታ .................. 3

ሐ. በ1979–1981 የሦስት ዓመት ዕቅድ የሚተኮርባቸው
አጠቃላይ ዓላማዎችና ስልቶች ..................... 21

መ. የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት.................. 28

ሠ. የክፍላተ ኢኮኖሚ ዕቅድ አጠቃላይ ይዘት................ 33

ረ. የ1979–81 የሦስት ዓመት ዕቅድ አቀራረብ........... 35

ሰ. ችላኑ የሚሸፍናቸው ክፍላተ ኢኮኖሚ................... 36

ሸ. ዕቅዱ የሚያስፈጽሙ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ............... 37

ቀ. የምርትና የአገልግሎት ግቦች አጣጣሉና እነዚህን ለማሟላት
የሚያስፈልጉት አቀራረብ ........................ 38

በ. የ1979– 81 ዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓት ............ 47

ማ ጠ ቃ ለ ያ ......................... 51

መመሪያ ከዚህ በታች ቀርቧል:: መመሪያው የአከናዋኙን ተወካይ ሁኔታና የሦስት ዓመት ዕቅዱ የሚያተኩርባቸውን አጠቃላይ ዓላማዎችና በሴቶች የሚያመለክትና እንዲሁም የዕቅዱን የአዘገጃጀት ዘዴና የአቀራረብ ሥርዓት የሚያብራራ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ በዕቅዱ ዘመን የሚጠበቀው የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት መጠን ቀርቧል::

4. የዕቅዱ ተግባራዊነትን ከሚወስኑት ሁኔታዎች ዋነኛው በዝግጅት ወቅት የሚኖረው የሥራ ጥራት ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ የዕቅዱ አቅራቢ አካል ዕቅዱን በተሰጡት መመሪያዎች ላይ በመመስረት በጥራት እንዲያዘጋጅ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤትም በዕቅዱ ዝግጅት ተከታታይ አካላት በዕቅዱ አዘገጃጀት የሚገጥማቸውን ችግር በጋራ ለመፍታትና ስለመመሪያዎቹ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመስጠት ያልተቋረጠ ትብብር ያደርጋል::

ከፍ ለማድረግ እንዲቻል የውጭ ብድር በአነስተኛ ወለድና በረጅም የክፍያ ዘመን እንዲሁም ከክፍያ ግዴታ ነፃ የሆነ ዕርዳታ እንዲገኝ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ። በተጨማሪ የውጭ ብድር አጠቃቀም የዕዳ መክፈል አቅምን ከማኅበር ጋር የተዛመደ መሆን ይገባዋል ።

9. ባለፉት ሁለት ዓመታት የደረሰው የግብርና ምርት ቅነሳ ያስከተለው ሌላው አሳሳቢ ሁኔታ የሀገሪቱን የምግብ እህል አቅርቦት አቅም እየተዳከመ መሄዱ ነው ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምግብ እህል ምርት /የብርዕ፣ የአገዳ፣ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ/ የቅነሳ አዝማሚያን ያሳየ ቢሆንም፣ በ1977 የተመረተው መጠን ባለፉት አምስት ዓመታት ከተመረተው አነስ ያለ ነበር ።

<u>የምግብ እህል ምርት ሁኔታ</u>

/1972 – 78/

| | የታረሰው መሬት መጠን<br>ሺ ሄክታር | የተገኘው ምርት መጠን<br>ሺ ኩንታል | የታየው ለውጥ /በመቶ/<br>በመሬት | <br>በምርት |
|---|---|---|---|---|
| 1972 | 6056.9 | 74955.8 | – | – |
| 1973 | 5676.9 | 65554.7 | –6.3 | –12.5 |
| 1974 | 5652.5 | 62905.8 | –0.4 | – 4.0 |
| 1975 | 6087.9 | 77981.1 | 7.7 | 23.9 |
| 1976 | 5733.0 | 63370.8 | –5.8 | –18.7 |
| 1977 1/ | 5587.4 | 44218.0 | –2.5 | –30.2 |
| 1978 2/ | 6351.6 | 76684.9 | 13.7 | 73.4 |
| 1972–76 /አማካይ/ | 5841.4 | 68953.6 | – | – |
| 1977–78 /አማካይ/ | 5969.5 | 60451.4 | 2.2 | –12.3 |

1/ ግምት

2/ ዕቅድ

## የመንግሥት እርሻዎች ምርታማነት

/ኩንታል/ ሄክታር/

| | 1970/71 | 1972–75 አማካይ | 1976 | 1977 ግምት |
|---|---|---|---|---|
| ስንዴ | 16.7 | 13.9 | 13.2 | 14.2 |
| በቆሎ | 33.5 | 26.2 | 19.2 | 23.1 |
| ማሽላ | 22.8 | 9.0 | 7.8 | 7.0 |
| ጥጥ | 21.7 | 20.7 | 17.2 | 21.9 |
| ቦሎቄ | | 4.0 | 3.3 | 3.0 |
| አኩሪ አተር | 8.4 | 3.6 | 2.3 | 3.3 |
| ጎመንዘር | 4.3 | 5.8 | 9.3 | 5.3 |
| ገብስ | | 17.7 | 13.0 | 13.0 |
| ሰሊጥ | | 1.5 | 3.4 | 0.1 |

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የመንግሥት እርሻዎች ምርታማነት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑንና ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ መምጣቱን ነው::

15. በአጠቃላይ በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሳ የሀገሪቱ የግብርና ምርት በተለይ የምግብ እህል ምርት በቂ ባለመሆኑ ሀገሪቱ በውጭ አገር የምግብ እህል ዕርዳታና ገቢ ላይ ጥገኛ እንድትሆን አስገድዷታል:: በየዓመቱ በተለይ በአሁኑ ወቅት ከውጭ አገር የገባ እህል በከፍተኛ መጠን ከተለያዩ ምንጮች በእርዳታ መልክ ወደ አገር ውስጥ ከሚገባው ባሻገር፣ ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ወጪ በማድረግ በየዓመቱ የምትገዛው መጠን በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ይህ የምግብ እህል ገቢ በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ በሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ጫና ቀላል እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ለምሳሌ በብሔራዊ ባንክ መረጃ በ1976 የውጭ ምንዛሪ ክምችት 136.4 ሚሊዮን ብር ያህል የነበረ ሲሆን በ1977 47.7 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ 1533.6 ሺ ኩንታል ስንዴ ከውጭ አገር ተገዝቷል::

4ኛ/ <u>በሽሌስት የምርት ግንኙነትን ማዳበርና ማጠናከር</u>

6. እስካሁን በሽሌስት የምርት ግንኙነትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በየሳሉ ጽዲገጠት ጥረት ተደርጓል :: ይሁንና በአሁኑ ጊዜ በገጠርም ሆነ በከተማ የተቋቋሙት የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በዙዎቹ በአደረጃጀትና በአመራር በኩል በርካታ ችግሮች ገጥሞአቸዋል :: በተጨማሪም መንግሥታዊ ድርጅቶች የአስተዳደርና የማኔጅመንት ድክመቶች ይታዩባቸዋል :: ስለዚህ በተለይ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በጥራትና በብዛት ለማቋቋምና ለማጠናከር መንግሥታዊ ድርጅቶችን አመራርና የሥራ ቅልጥፍና ለማሻሻልና እንዲሁም በየኢኮኖሚ መስኩ ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ የተጀመረው ጥረት በተጠናከረ መንገድ ይቀጥላል ::

5ኛ/ <u>የሥራ ስምሪት ዕድልን ማስፋፋት</u>

7. ሀገሪቱ ካሉባት አሳሳቢ ችግሮች አንዱ በከተሞች ያለው የግልጽ ሥራ አጥነት መጠን ከፍተኛ መሆን ነው :: ይህ ችግር በተለይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ባጠናቀቁ ግለሰቦች ላይ ፀንቶ ይገኛል :: ሥራ አጥነት የገቢ ክፍፍል መዛባትን፣ የሀብት መባከንንና የገበያ ጥበትን በእነዚሁም ምክንያት የልማት ወገታትንና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ድክመቶችንና ቀውሶችን የሚያመለክት ቢሆን ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች መንስዔ በመሆን ዓይነተኛ ሥፍራ ይዞ ይገኛል :: ስለዚህ በሦስት ዓመቱ ዕቅድ ዘመን ለዚህ ዐቢይ ችግር ደረጃ በደረጃ መፍትሔ የማስገኘት ጥረት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል ::

6ኛ/ <u>የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮችን ማቃለል</u>

8. የዚህ ዓላማ ይዘት አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን፣ አካለስንኩላንን፣ ቦዘኔነትን፣ ዝሙት አዳሪነትና ማይምነት መሰሉትን የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች ለማስወገድ

2. <u>የምግብ እህል ምርትን ለማሳደግ</u>

- የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን አቅርቦት ማሻሻል
- በግብርና ዘዴ የሥልጠና ፕሮግራም ማካሄድ
- የአነስተኛ መስኖ ልማት ሥራ በስፋት እንዲቀጥል ማድረግ
- የግብርና ምርትን የሥርጭትና ግብይት ሥርዓት ማሻሻል

3. <u>የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማስፋት</u>

- ለውጭ ገበያ የሚቀርቡትን ነባር ምርቶች መጠንና ጥራት ማሳደግና ማሻሻል
- የማዕድን ውጤቶችን ለውጭ ገበያ ማቅረብ
- ሰፊ የሆነውን የሀገሪቱን የእንስሳት ሀብት በማልማት እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች በውጪ ገበያ ያላቸው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ
- በተለይ የፕሮጀክት አዘገጃጀት አቅምን በማጠናከር የውጭ ብድርና ዕርዳታ ግኝትንና የመጠቀም ችሎታን ማዳበርና ማሻሻል
- ከውጭ የሚመጡ ሸቀጦችን፣ ለምሳሌ ጨዉ፣ ከናፍ፣ ተምባሆና ሌሎችም በተቻለ መጠን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት

4. <u>ድርቅንና የሚያስከትላቸውን ችግሮች ለመቋቋም</u>

- በየአካባቢው በተለይ በተደጋጋሚ ድርቅ በሚከሰትባቸው ክፍላተ ሀገር የበረሀ አየር ጠባይ ሊያቆሙ የሚችሉ ዛፎችን በመትከል የደን ልማት ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል፤
- በተፈጥሮ ሊያቆጠቁጡ ሊያገግሙ የሚችሉ አካባቢዎች መከለልና መንከባከብ
- ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ የደንን ጥቅምና የደን መጨፍጨፍ የሚያስከትለውን ጉዳት በማስረዳት የደን መንከባከብና የዛፎች ተከላ ዘዴ በማስተማር በአጠቃላይ የደን ልማት የሕዝቡ ተግባርና ባሕል እንዲሆን ማድረግ
- የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ በተጠናከረ መንገድ እንዲቀጥል ማድረግ
- የሠፈራ ፕሮግራምን ማካሄድ
- የመስኖ ልማት ሥራን ማካሄድ

5. <u>የበሽሌበት የሥራ ግንኙነትን ለማቃበርና ለማጠናከር</u>

- የገበሬዎችንና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋምና ማጠናከር
- የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋቋምና ማጠናከር
- በየክፍላተ ኢኮኖሚው ውስጥ የመንግሥት ድርሻን ማሳደግ
- ገበሬው አመቺ በሆነ ቦታ በመንደር ተሰባስቦ እንዲኖር ማድረግ
- ዘላኑን ሕብረተሰብ በማኅበር ተደራጅቶ በተወሰነ ቦታ ሰፍሮ የግብርና ሥራን እንዲለማመድ ማድረግ
- ሰፊው ሕዝብ በድርጅቶቹ አማካይነት በልማት ሥራ እንዲሳተፍ ማድረግ

6. <u>የሥራ ስምሪት ዕድልን ለማስፋፋት</u>

- በየክፍለ ኢኮኖሚው በተቻለ መጠን በሰው ኃይል በበለጠ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን መርጦ ሥራ ላይ ማዋል
- የዕደ ጥበብና አነስተኛ ኢንዱስትሪን በማስፋፋት የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ማድረግ
- የውጭ ኢንቬስትመንት /የጋራ የልማት ማኅበር/ የኢኮኖሚውን የማምረት አቅም ለማሳደግና የሥራ ስምሪት ዕድል ለመፍጠር ስለሚያስችል የጋራ ልማት ማኅበር አዋጁን ተግባራዊ ማድረግ

7. <u>ማኅበራዊ የኑሮ ችግሮችን ለማቃለል</u>

- ከሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ዝሙት አዳሪዎችና ቦዘኔዎችን በተሟላ ሥልጠና በማብቃት በምርት ሥራ እንዲሠማሩ ማድረግ
- ያሉትን የአካል ስንኩላን ማሠልጠኛ ተቋሞችን በማጠናከር አካለ ስንኩላን በምርት ተግባር እንዲሠማሩ ማድረግ

- በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግር ምክንያት ያለ አሳዳጊና ሰብሳቢ ለቀሩ ሕፃናትና ወጣቶች ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት።
- ግለሰቦችና የቤት ሕብረት ሥራ ማኅበራት በመኖሪያ ቤት ሥራ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት። ለዚህም አስፈላጊውን የቴክኒክና የፊናንስ ድጋፍ መስጠት
- የቤት መሥሪያ ዕቃዎች የዋጋ ንረት በተቻለ መጠን መግታት
- ለቤቶች ሥራ እንቅስቃሴ አመቺ ያልሆኑትን የቦታ አሰጣጥ ሥርዓቶች፣ የባንክ ብድር ደንቦችና ሥርዓቶች እንዲሻሻሉ ማድረግ
- በመንግሥት በየደረጃው የሚሠሩት ቤቶች ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ

8. <u>የግብርና ምርምርና ሥርፀትን ለማጠናከር</u>

- የግብርና ምርምር ተቋሞችን ማደራጀትና ማስፋፋት
- ተመራማሪዎችን በብዛት ማፍራት
- ከውጭ የምርምር ድርጅቶች ጋር ግንኙነትና ትብብርን መፍጠር

የተጠቀሰው የበጤራ ፬ ኢኮኖሚ የዕድገት ዘመን እውን ለማድረግ ባጠቃላይ በሦስቱ ዓመት ዕቅድ ዘመን ውስጥ የ5.5 ቢሊዮን ብር ጅሬ ኢንቨስትመንት መደረግ እንዳለበት ተገልጿል። ይህንን የኢንቨስትመንት መጠን ለማሟላት ሊደረግ የሚቻለው የሀገር ውስጥ ቁጠባ ለሦስቱ ዓመት ባጠቃላይ 2.13 ቢሊዮን ብር ብቻ እንደሚደርስ ስለተገመተ በተጨማሪ 3.4 ቢሊዮን ብር የሚሆን የተጣራ የውጭ አገር ብድርና ዕርዳታ መገኘት ይኖርበታል። በተለይ የሀገር ውስጥ ቁጠባ መደረግ ካለበት የኢንቨስትመንት መጠን አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ በመሆኑ በሦስቱ ዓመታት ከሚገኘው ጠቅላላ ተጨማሪ ምርት 15 በመቶው መቆጠብ ስለሚኖርበት ይህንኑ እውን ለማድረግ ጠንካራ የፖሊሲ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል።

ሠ. <u>የክፍላተ ኢኮኖሚ ዕቅድ አጠቃላይ ይዘት</u>

የ1979–81 ዕቅዱ ክፍላተ ኢኮኖሚና ዘርፎች የሚያወጧቸውን ፕላኖች በማጠቃለል፣ የዘርፉ ውስጥና ዘርፎች መካከል ያለውን ዝምድና ተመጣጣኝነት በማስተካከልና እንዲሁም በአጠቃላይ ሊገኙ ከሚችሉት፣ ፕላኑን ለማስፈጸም ከሚያስፈልጉት የሰው፣ የቁሳቁስና የገንዘብ ኃይል ጋር በማገናዘብ የሚቀርብ ነው። ይህም በመሆኑ፣ ለማጠቃለልና ለማዘጋጀቱ እንዲረዳ ክፍላተ ኢኮኖሚና ዘርፎች የሚያቀርቧቸው ዕቅዶች ተመሳሳይ አቀራረብና ይዘት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት የየክፍለ ኢኮኖሚውን የየዘርፉ ዕቅዶች የሚከተሉትን ዐበይት ነጥቦች የሚያቅፉ ይሆናሉ።

1ኛ/ ክፍለ ኢኮኖሚው ወይም ዘርፉ ባለፉት የቅርብ ዓመታትና በአሁኑ ጊዜ ስለአለበት ሁኔታ ግምገማ፣

ሀ. ባሉት መረጃዎች መሠረት በ1975 – 78 የተከናወነው ሥራ ከታቀደው ጋር በማወዳደር፣

ለ. የገጠሙት ዐበይት ችግሮችና የተወሰዱት እርምጃዎች።

2ኛ/ ዓላማዎች፣

3ኛ/ ሥልቶች፣

– በዚህ ርዕስ ሥር ምርትን ለማሳደግ በሥራ ላይ የሚውሉት ዘዴዎች /የሠራተኛ ምርታማነትን ማሳደግ፣ የመሬት የማምረት ኃይልን ከፍ ማድረግ፣ ትርፍ የኢንዱስትሪ የማምረት ኃይልን በምርት ተግባር ላይ ማሠማራት፣ የሥራ ፈረቃዎችን መጨመር፣ ተጨማሪ ሠራተኞችን መቅጠር፣ ተጨማሪ የማምረቻ መሣሪያዎችን መትከል፣ ተጨማሪ መሬት ማረስን ወዘተ.../ ያጠቃልላሉ።

4ኛ/ የምርት የአገልግሎት ግቦች፣

- በዚህ ርዕስ ሥር እያንዳንዱ የሚታቀደው የእርሻ ሰብል፣ የኢንዱስትሪ ውጤት፣ የሚከፋፈለው ሰብል ወይም ውጤትና እንዲሁም ሌሎች የታቀደው አገልግሎት በመጠንና በዓይነት ይቀርባሉ ::

5ኛ/ ግቦችን ለማሟላት የሚያስፈልጉት

ሀ. የሰው ኃይል

ለ. ማቴሪያል

- መሠረታዊ ማቴሪያሎች /ለምሳሌ ሲሚንቶ፣ ነዳጅ፣ ወዘተ./

ሐ. ገንዘብ /በሀገር ውስጥ ብርና በውጭ ምንዛሬ በዶላር/

6ኛ/ ቋሚ ኢንቨስትመንት (fixed capital formation)

- የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የትራንስፖርት መሣሪያዎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ መኖሪያ ያልሆኑ ሕንፃዎች፣ ሌሎች የግንባታ ሥራዎች፣ የቢሮ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፣ ለመሬት ማሻሻያ፣ ለርቢና ለሰበት (draught) ለእንስሳትና ለፍራፍሬ ተክሎች ዝግጅት፣

7ኛ/ የኢንቨስትመንት፣ የምርትና የአገልግሎት ክፍለሀገራዊ ስርጭት፣

8ኛ/ የምርት፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና መንግሥት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍለ ሀገራዊ ሥርጭት፣

9ኛ/ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ በሥራ ለመተርጎም የሚወሰዱ የፖሊሲና ድርጅታዊ እርምጃዎች፣

10ኛ/ የክፍለ ኢኮኖሚ ዝርዝር የክንውንና የዕቅድ ስታትስቲክስ ያዘለ ::

ረ. የ1979-81 የሦስት ዓመት ዕቅዱ አቀራረብ

በሦስት ዓመት ዕቅዱ ወቅት ሊሠሩ የታቀዱት ፕሮጀክቶች የምርትና, የአገልግሎት ገቢ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹንና ገበያን ለማስፈጸም የሚያስፈልገው ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና ማቴሪያል በሥራ በሦስት ዓመትና በእያንዳንዱ ዓመት ተከፋፍለው በሚከተለው ዓይነት ቀርበዋል::

| | 1979 | 1980 | 1981 | 1979-80 |
|---|---|---|---|---|
| ለምሳሌ፣ | | | | |
| /የምርት ገቢ/ ሲሚንቶ /ቶን/ | 56000 | 61000 | 61000 | 178000 |
| /የአገልግሎት ገቢ/ ማጓጓዣ | | | | |
| ሺ ኩንታል | 2900 | 3800 | 4900 | 11600 |
| /ፕሮጀክት/ ገልገል ጊቤ | | | | |
| ው.ኃ.ማ /ሺ ብር/ | 18000 | 40000 | 70000 | 128000 |
| የኢንቨስትመንት ወጪ /ሺ ብር/ | 5900 | 10700 | 12900 | 29500 |

የዚህ ዓይነት አቀራረብ በተለይ የ1979 ዓመታዊ ዕቅድን ለበጀቱ በተለየ ደከሚነት አዘጋጅቶ ለማውጣት ጊዜ ስለማይኖር በ1979 የሚሠራውን ሥራ ለይቶ ስለሚያሳይ፣ በሦስት ዓመት ዕቅዱ ውስጥ የተመለከተውን የ1979 ዕቅድ ማስፈጸሚያ በጀት በቀላሉ ለማዘጋጀት ያስችላል::

ለ. ጎልቶ የሚሸፍኑ ዋና ክፍለ ኢኮኖሚ፣

በዓላማው ሰፊ ለገበሬናት ለሠራተኛ ለውሃ ለማትና ለውጭ ንግዱ ዘርፎች የተለየ ትኩረት አገልግሎት የተወሰነ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የሚዘጋ ጁት የሰማት ዕቅዶች ሁሉ ለቀድ ማለት ሁሉንም ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያቅፉ አገራ ዊ ሆና ነው የ1978 ዕቅዱ የሚጠቃለሉትን ክፍለ ኢኮኖሚ ይሸፍናል::

1. ግብርና
2. ኢንዱስትሪ
3. ማዕድን
4. ኢነርጂ
5. ውሃ ልማት
6. ትራንስፖርትና መገናኛ
7. ኮንስትራክሽን
8. ንግድ
9. ቱሪዝምና ሆቴሎች
10. ከተማ ልማትና ቤት
11. ትምህርት
12. ጤና
13. ማኅበራዊ ኑሮ ደኅንነት
14. ባህል
15. አካል ማሠልጠኛና ስፖርት
16. ማስታወቂያ
17. ሳይንስና ቴክኖሎጂ
18. የሰው ኃይል
19. ፋይናንስ /ባንክና ኢንሹራንስ ጭምር/

## ፬. <u>የምርትና የአገልግሎት ግቦች አጣጣልና እነዚህን ለማሟላት የሚያስፈልጉ አቀራረብ</u>

### ፬.፩ <u>የግቦች አጣጣል</u>

1. ግቦች በዋጋ ወይም በመጠን የተገለጹ ዓላማዎች ናቸው ማለት ይቻላል ። ለምሳሌ "የምግብ ምርትን ማሳደግ" የሚለው ዓይነ ዓላማ በምን ያህል? የሚለው ጥያቄ የሚመለሰው በአመዛኙ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና በገጠር ክፍለ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚወረቱ የምግብ ውጤቶች እንዲሁ ግቦችን በመጣልና እነዚህንም በተጨባጭ ለማስገኘት የሰው ኃይልን፣ ገንዘብንና ማቴሪያልን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ በማቀናጀት በምርት ተግባር በማሰማራት ነው ። ምንም እንኳን የአንዳንድ የልማት ዓላማዎች ይዘት ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ሙሉ በሙሉ በአኃዝ ለመግለጽ የሚያስቸግር ቢሆንም፣ ለአብዛኛዎቹ የልማት ዓላማዎች አኃዛዊ ግቦችን መጣል በመቻሉም በላይ እነዚህ ዓላማዎች ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት አኃዛዊ የምርትና የአገልግሎት ግቦችን በመጣልና በማስፈጸም ብቻ ነው ።

2. የምርትና የአገልግሎት ግቦች ከመጣላቸው በፊት የሚከተሉት ዓበይት የኢኮኖሚ ገጽታዎችና ትንተናዎች መደረግ ይኖርባቸዋል ።

1ኛ/ ባለፉት የቅርብ ዓመታት በተለይም ባለፈው የሃያ ዓመት በአጠቃላይ የክፍለ ኢኮኖሚው ወይም የገጠር ክፍለ ኢኮኖሚው ሥራ ክንውን ሁኔታ፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ችግሮችን ለማቃለል ወይም ለማስወገድ የተወሰዱ እርምጃዎች፣ እነዚህ እርምጃዎች ለደረሱት የሚፈጥሩት አወንታዊ ሁኔታ፣ በክፍለ ኢኮኖሚውን በሚመለከት በማዕከላዊ መንግሥት የተወሰዱና የሚወሰዱ የፖሊሲ እርምጃዎች፣ የሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ የሥራ ክንውን ሁኔታ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ ክፍለ ኢኮኖሚውን በሚመለከት የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ የሚኖረው

/ቤት ማቆሚያ፣ ውሃ፣ መብራት፣ ከቤቱ ጋር የተያያዘ ማበልጸጊያዎች፣ ወዘተ.../
የሚወጡ ወጪዎች የሚገኙ ሰሀን፣ መኖሪያ ቤት ፈርኒቸርና የቤት ዕቃዎች
አደገኙ፣

2ኛ/ መኖሪያ ያልሆኑ ሕንፃዎች

የፋብሪካ ሕንፃዎች፣ መጋዘኖች፣ የቢሮ ሕንፃዎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ሆቴሎች፣ ጋራዦች፣ በረቶች፣ የሃይማኖት፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመዝናኛ ሕንፃዎች፣ ወዘተ.. እና የሕንፃዎች አካል የሆኑ ቋሚ ንብረቶች፣

3ኛ/ የኮንስትራክሽን ሥራ/ከመሬት ማልማት ሌላ/

የባቡር መስመሮች፣ መንገዶች፣ የፍሳሽ ማስተላለፊያዎች፤ ድልድዮች፣ የመሬት ውስጥ መንገዶች፣ ወደቦችና ወደብ-ነክ የኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ አይሮፕላን ማረፊያዎች የቧንቧ መስመሮች፣ የነዳጅና የማዕድን ጉድጓዶች፣ ካናሎች፣ የውሃ ኃይል ጣቢያዎች፣ ግድቦች /ከመስኖ ጋር ያልተያያዘ/ የስፖርት ሜዳዎች፣ የኤሌክትሪክ ማሰራጫ መስመሮች፣ የነዳጅ ቧንቧዎች፣ የቴሌፎንና የቴሌግራፍ መስመሮች ወዘተ...

4ኛ/ መሬት ማልማትና ቋሚ ተክል

የመሬት ምንጣሮ፣ የመስኖና ኩሬ መቆጣጠሪያ ግድቦች፣ ደን ተከላ፣ ወይንና ምርት መስጠት እስከሚጀምሩ ለቋሚ ተክሎች /የቡና፣ የሻይ፣ የፍራፍሬ፣ ወዘተ... ተክሎች/ የሚወጣ ወጪ፣

5ኛ/ የትራንስፖርት መሣሪያዎች

መርከቦች፣ አይሮፕላኖች፣ የባቡር ፉርጎዎች፣ የጭነትና የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች፣ ጋሪዎች ወዘተ...

6ኛ/ የቢሮ ዕቃዎችና መሣሪያዎች

የቢሮ ፈርኒቸር፣ የጽሕፈት መኪናዎች የፎቶ ኮፒ መሣሪያዎችና ሌሎች የቢሮ መሣሪያዎች፣

7ኛ/ የማሽነሪ መሣሪያዎችና ዕቃዎች

የእርሻ ትራክተሮች፣ ኮምባይነሮች፣ መውቂያዎችና ሌሎች የእርሻ መሣሪያዎች፣ የኃይል ማመንጫ መሣሪያዎች፣ የኢንዱስትሪ ማሽነሪ መሣሪያዎች፣ የማዕድንና የኮንስ

ተራክሸን መሣሪያዎች፣ የሆቴል ዕቃዎችና መሣሪያዎች፣ የሆስፒታል የትምህርት ቤት፣ የኮርኮር መሣሪያዎችና ዕቃዎች ወዘተ..

8ኛ/ <u>የርቢና የስብት እንስሳት</u>

ለርቢ፣ ለእንስሳት ተዋፅኦና ለስብት የሚሆኑ እንስሳትን እንደ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ሲወጠን የሚከተሉት ዐበይት ሁኔታዎችን ማጤን ያስፈልጋል።

1ኛ/ ኢንቨስትመንቱ የሚያስገኘው ምርት ወይም አገልግሎት በማዕከላዊ ፕላኑ ውስጥ ቅድሚያና ትኩረት መሰጠቱን፣

2ኛ/ ኢንቨስትመንቱ በሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ላይ መመሥረቱን፣

3ኛ/ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልገው የቴክኖሎጂ ዓይነት የሥራ ሥምሪቱን የሚያስፋፋ መሆኑን፣

4ኛ/ የውጭ ምንዛሬን መቆጠቡ ወይም ማዳኑ፣

5ኛ/ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልገው ወጪ የሚሸፈነው ከየት ምንጭና በምን ሁኔታዎች እንደሆነ፣

6ኛ/ ከሌሎች አማራጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር ሲወዳደር ያለው አዋጭ፣

7ኛ/ ኢንቨስትመንቱ የሚያስከትለው ገቢና ወጪ፣

8ኛ/ ኢንቨስትመንቱ አትራፊ መሆን አለመሆኑ፣ በገንዘብ መልክ አትራፊ ባይሆንም በአጠቃላይ የሰጠና የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ያለው ሚና፣

በሌላ አነጋገር ከተጠቃሹ ሁኔታ የራቁ የኢንቨስትመንት ዕቅዶች ማቅረብን ለማስወገድ በተለይ የሚከተሉትን ተግባሮች ማከናወን ያስፈልጋል።

1ኛ/ ከላይ በተጠቀሱት መመዘኛዎች /ኢንቨስትመንቱ በሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ላይ መመሥረቱ ወዘተ../ መሠረት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ቅደም ተከተል ማውጣት፣ በዚህ መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለዘገቡ አስፈላጊ ከሆኑ ለሠራዙ የሚችሉትን ለይቶ ማውጣት፣

2ኛ/ የዕጢያ ከሚሰጧቸው መካከል ሥራቸው በመካከሉ ላይ ላሉት፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ወይም ከገጠሬት የተሰበሰቡትና ትናንታቸው ሥራ በሥራ ላለ ቀላቸውና የገንዘብ ምንጫቸው በለበት ማግኘ ሁኔታ ለታወቀላቸው ትኩረት መስጠት፣

3ኛ/ ከሀገሪቱ የገንዘብ ሀብት /የውጭ ምንዛሬ ጭምር/፣ የሠለጠነ የሰው ኃይሎች ሊገኙ ከሚችሉት ዓይነቶች፣ የከገበትራበጠን ለየዶች፣ ድርጅታዊ ችሎታ፣ ወዘተ.. አገባር በዕቅዱ ዘመን በየደረጃው ሥራቸው ሊከናወን የሚችሉትን ፕሮጀክቶች ብቻ በዕቅዱ አገኙታቸው ማድረግ፡፡

ቁ.3 <u>የሰው ኃይል ፍላጎት አወሳሰን</u>

8. የሰው ኃይል ፍላጎትን ከሚወስኑት መካከል የሚገኙት የምርትና የአገልግሎት ግቦች መጠን፣ የአመራረት ዘዴና የሠራተኛ ምርታማነት ዕድገት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአንድ በኩል የአመራረት ዘዴን በተቻለ አቅም ይበልጡኑ የሰው ኃይልና የሚያሠማራ በማድረግ የሥራ ዕድሎችን ለማስፋፋት ያለውን ዓላማ ለማሟላት በየክፍለ ኢኮኖሚው በየዘርፉ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የነፍስ ወከፍ ምርትን በማሳደግ የተጣሉትን ግቦች በአነስተኛው ወጪ በማሟላት የአምራች ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ተርፋማነት ብሎም ዘላቂነት ያለው /viable/ የኢኮኖሚ ሕብረተሰብን ማረጋገጥ አማራጭ የሌለው የአመራረት ሥልት ነው፡

9. ከእነዚህ መሠረታዊ አስተሳሰቦች በመነሳት የሰው ኃይል ፍላጎትን ለመወሰን የሚከተሉትን ዐበይት ሁኔታዎችን ማጤን ያስፈልጋል፤

1ኛ/ በኘላን ዓመት መጀመሪያ /በ1976፣ በ1977 እና በ1978/ ላይ የነበረው የሠለጠነና ያልሠለጠነ የሰው ኃይል ብዛት፣

2ኛ/ በእነዚሁ ሶስት ዓመታት የተመረተውን ምርት ወይም የተሰጠው አገልግሎት መጠን፣

3ኛ/ የሠራተኛ ምርታማነት ዕድገት ሁኔታ

4ኛ/ የአመራረት ዘዴ ለውጥ፣

5ኛ/ በዕቅዱ ዘመን /በ1979–81/ በሌሎች ሌሎች ምክንያት ከሥራ
የሚገለሉ ሠራተኞች ብዛት፣

6ኛ/ የሠራተኛ ምርታማነትና ዕድገትና የአመራረት ዘዴ ለውጥ
በሰው ኃይል ፍላጎት ላይ የሚያስከትለው ለውጥ፣

ቀ.4 <u>የማቴሪያል ፍላጎት አወሳሰን</u>

10. የማቴሪያል ፍላጎት ከሚወሰኑት መካከል ዋናዎቹ የሚሰሉት የምርትና የአገልግሎት ግቦችና እንዲሁም ከተወሰነ የማቴሪያል መጠን ሊገኝ የሚችለው የምርት መጠን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአሠራር ሥልት ጉድለት፣ ከአከማቻቸት ጉድለት፣ ከተበላሹ ወይም ከአረጁ የማምረቻ መሣሪያዎችና ከሌሎች መንስዔዎች የሚደርሰው የማቴሪያል መባከን ወይም ብልሽት የማቴሪያል ፍላጎትን ከፍ የሚያደርግ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ሊደርስ የሚችለውን የማቴሪያል መባከን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ የማቴሪያል ፍላጎትን ለመወሰን ከእነዚህ መሠረታዊ አስተሳሰቦች መነሳትና የሚከተሉትን ትንተናዎች ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

1ኛ/ በኋለኛው ዓመት መጨረሻ /በ1976፣ በ1977 እና በ1978/
የነበረው የዋና ዋና ማቴሪያሎች ክምችት(stock) መጠንና
ዋጋ (value)

2ኛ/ ለእያንዳንዱ ዓይነት ምርት የሚያስፈልገው የማቴሪያል ፍጆታ፣

3ኛ/ ከዓይነት ምርት የማቴሪያል ፍጆታ አንፃር የተሰሉትን የምርትና
የአገልግሎት ግቦች ለማሟላት የሚያስፈልጉት ዋና ዋና ማቴሪያ
ሎች መጠንና ዋጋ፣

ቀ.5 የሳይንስና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፤

11. ከሀገሪቱ የልማት ዓላማ ጋር በተጣጣመ መንገድ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሚያስችሉትን ዐበይት ሁኔታዎች ግልን ያስፈልጋል፤

1ኛ/ በበኩል ኢኮኖሚው ያለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና ሥርፀት ችሎታና በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚገኙ ምርምር ውጤቶች የመጠቀም አቅም፤

2ኛ/ ወደሀገር የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በመሠረታዊ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ሽግግር፤ የሥራ ዕድል በማስፋፋትና በውጭ ምንዛሪ በማዳን ወይም በመቆጠብ ረገድ የሚኖራቸው ውጤት፤

ቀ.6 የፋይናንስ ፍላጎት አወሳሰን

12. ፋይናንስ /ገንዘብ/ የሰው ኃይልን ለመቀጠርና ለመደበኛ ምርትና ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ለመግዛት የሚያስችል መሣሪያ በመሆኑ፤ የሚፈለገው የገንዘብ መጠን የሚመሠረተው በሚገኙት የምርትና የአገልግሎት ግቦች፤ በሥራ ምርታማነት፤ በዋጋ ዕድገትና በመሣሪያ የአጠቃቀም ቅልጥፍና ላይ ነው። የፋይናንስ ፍላጎት ለመወሰን የሚያስችሉትን ትንተናዎች ማድረግ ያስፈልጋል።

1ኛ/ ባለፉት የቅርብ ዓመታት /በ1976፤ በ1977 እና በ1978/ የነበረው የመደበኛና የካፒታል /የሥራ ማስኬጃና የኢንቨስትመንት/ ወጭ፤

2ኛ/ በእነዚሁ ዓመታት የተከናወነው ሥራ መጠን፤

3ኛ/ በሚቀጥለው የዕቅድ ዘመን የሚጠበቀው የዋጋ ጭማሪ፤

4ኛ/ ለፕላኑ ዘመን የሚያስፈልገው ገንዘብ ምንጭ /ከመንግሥት በጀት፤ ከውጭ ብድር ወዘተ.../፤

## ፱.7 የምርትና የአገልግሎት ዋጋ ስሌትና የመረጃ አቀራረብ

13. የ10 ዓመቱ ዕቅድ የዋጋ መሠረት ዓመት (base year) 1973 ዓ.ም. በመሆኑ እንዲሁም ለበጀት ሥራና ለሌላ የኢኮኖሚ ትንተና አስፈላጊ በመሆኑ የ1979–81 ዕቅድ የምርትና የአገልግሎት ገቢ በ1973 ዋጋ የሚቀርቡ ሲሆን፣ የኢንቨስትመንት ገቢና ሌሎች አኀዞች ደግሞ የሚቀርቡት በጊዜው ዋጋ ይሆናል:: በተመሳሳይ የ1976ና የ1977 ተከለሰና ክንውንና የ1978 የክንውን ግ/ት አኀዞች በ1973 ዋጋ ማሳየት አስፈላጊ ነው:: የዕቅዱም ሆነ የክንውን አኀዞች በመጠንም በዋጋም (value) መቅረብ አለባቸው:: በመሠረቱ አጠቃላይ የዕቅድ ገጽታዎችን የሚያሳዩ ዝርዝር መረጃዎች የሚቀርቡት በየፕላን አስተዳደር ደረጃው በሚቀርቡ ተመሳሳይነት ባላቸው የዕቅድና የአፈጻጸም ማቅረቢያ ቅጾች ነው::

## በ. የ1979 – 81 ዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓት

### በ.1 አጠቃላይ ሥርዓት

1ኛ/ በማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጡትን የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያዎችን፣ የምርትና የአገልግሎት እንዲሁም የኢንቨስትመንትና የፋይናንስ መነሻ ግቦችን መ/ቤቶችና ድርጅቶች በሥራቸው በየደረጃው ለሚገኙ ድርጅታዊ እርከኖች በማስተላለፍና በማሳበር እንዲሁም ክፍለ ኢኮኖሚያቸውን ወይም ዘርፋቸውን በሚመለከት ከፕላን ግብና የሚቀርቡትን የግብና የፕላን ሃሳቦች በማቀነባበርና በማዋሃድ ክፍለ ኢኮኖሚያቸውን ወይም ዘርፋቸውን በሚመለከት የሴክተርና የክፍለ ሀገር ገጽታዎች ያሉዋቸው ዕቅዶች አዘጋጅተው ለማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣

2ኛ/ የማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት የቀረቡትን የዕቅድ ሀሳቦች ሊገኝ ከሚችለው የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የማቴሪያል ሀብት፣ ከአጠቃላይ ዓላማዎችና ሥልቶች፣ ባላቸው የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት ክ/ሀገርን ለማልማት ካለው ዓላማ አኳያ፣ ከማዕከላዊ ደረጃ ከተሰጡት የምርትና የአገልግሎት፣ የኢንቨስትመንትና የፋይናንስ መነሻ ግቦች አንፃር ከገመገመና በክፍለ ኢኮኖሚ መካከል ያለውን ተዛምዶ ከመረመረ በኋላ አስፈላጊዎቹ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ መመሪያ ይሰጣል ፡፡

3ኛ/ የክፍለ ኢኮኖሚ ዕቅዶች ክለሳና እርማት ከተደረገባቸው በኋላ በማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ እንደገና ታይቶና ተቀነባብሮ የ1979 – 81 ዕቅድ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ይፀድቃል ፡፡

የሰዓት ሥርዓቶች የወጡ ንገጾና የሌሎች አገልግሎቶች ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጾች ሲሆኑ፣ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎችንም እንደአስፈላጊነቱ በኋላ ክፍና ፍ/ቤቶችና በክፍላተ ሀገሮች ወረዳዎች በኩል እየተጠየቁ የሚቀርቡ ይሆናሉ። እያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ አቅራቢ ፍ/ቤት ወይም ፎርሞቹ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙትንና ኋላም በተከታታይ የሚላኩትን ቅጾች በሚገባ ቀድቶ ለማዕከሉ ጊዜ በሥራ ላይ ከሚገኘው ጽ/ቤት በወቅቱ መላክ አለበት። ቅጾቹ ለወሳኝ የሚያገለግሉ በመሆኑ ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዙ እንደመሆናቸው መጠን በጥንቃቄ ተሞልተው በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በተካቸው መፈረም አለባቸው። ቅጾቹን በመሙላት ረገድ አንዳንድ ጊዜ ከፍርድ ቤቶች የሥራ ጠባይ የተነሳ የተጠየቁትን መረጃ በተፈለገው አመዳደብና ዝርዝር ለመስጠት ፍጹም አስቸጋሪ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ሁኔታውን የሚያስረዳ የግርጌ ማስታወሻ በመስጠት ቅጹን ሞልቶ ማቅረብ ይቻላል። የተሟላ መረጃ ሲኖር ወይንም ተከታታሉ እንዲታረም ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም መለያየት ወይም በሪከርድ አያያዝ ሥልት ጉድለት ምክንያት እርስ በርስ የሚቃረኑ መረጃዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ በቅጾቹ ላይ የሚሰፍሩት መረጃዎች ትክክለኛነትና አስተማማኝነት በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል።

